# ፍትሕ የጠማው ህዝብ

## እስር ቤት የታጎሩት እስክድርና አንዱአለም ብቻ አይደሉም ነፃነቱን ተነጥቆ የታሰረው 85 ሚሊዮን ህዝብም ጭምር ነው

ክፍል 1

ይኩኖ መስፍን
ቦስተን ማሳቹሰት

አንድ ሰብኣዊ ፍጡር ከሌላው እንስሳዊ ፍጡር የሚለየው ምግብ በልቶ ውሃ ጠጥቶ በማደሩ አይደለም። ዋናው የልዩነቱ መሰረታዊ ሚስጢር በነፃ የመፃፍ፣ የመናገርና የመደራጀት መብቱንና ሕሊናዊ ነፃነቱን የመጠበቅ ሓይል ስላለው ብቻ ነው። የአንድ ዜጋ ስብእናውንና ህልውናውን የሚለካውንም እነዚህ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች በአግባቡ ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። በአንድ ሀገር ወይም በአንድ ሕብረተሰብ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የሰው ልጅ የነፃነት መብቶች እውን ለማድረግም ከዚህ በታች በጥቂቱ የተጠቀሱትን የአንድ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ባህርይ መገለጫ የሆኑትን መርሆዎች ተግባራዊ መሆን ወይም አለመሆን ይወስናሉ።

1. የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥ (መላ ዜጎች ያላንዳች አድልዎና ቂም በቀል፣ ያላንዳች ሽብርና ወከባ የሕግ ከለላና ሕገ መንግስታዊ ዋስትናቸው ሲረጋገጥ)
2. የህዝቡን መሰረታዊ ሰብኣዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብሩ ነፃ የፍትሕና የዲሞክራሲ ተቋማት ሲመሰረቱ (ህዝቡ የስልጣን ምንጭና ባለቤት ለመሆን ሲችል)
3. ህዝቡ ነፃ የብዙኃን መገናኛ ተጠቃሚ ሲሆን (ህዝቡ አማራጭ ሃሳብ ለመስማት፣ ለመተቸት፣ ለመጠቀምና አዲስ ነገር ለማመንጨት ዕድል ሲያገኝ)
4. መልካም አስተዳደር ሲኖር (ከሙሱና የፀዳ፣ የህዝቡን የጋራ እሴቶች የሚጠብቅ፣ ግልፅነት ያለውና ሃላፊነት የሚሰማው የህዝብ አገልጋይ መንግስት ሲመሰረት ነው)

ሁላችንም እንደምንሰማውና እንደምናየው ዛሬ በዓለማችን ዙሪያ በተለይም በሰሜን አፍሪቃና እንዲሁም በመካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች እየተካሄደ ያለው የህዝብ ዓመፅ መነሻው አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም ከላይ በከፊል የተጠቀሱትን የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች በአግባቡ ስላልተመለሱ ብቻ ነው። የዓመፁን ወላፈን እያየለና እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በሄደ ቁጥርም አምባ ገነኖች በትረ ስልጣናቸውን እየተናደና ጊዜውም እየመሸባቸው መሆኑን በውል ሲረዱ የፍትሕ እጦት የወለደውን የህዝቡን ብሶትና ቁጣ በውሸት አሊያም በሽብር ለማዳፈን ሲሉ ነፃነት በጠማው ህዝብ ላይ ምን ዓይነት ግፍና ደባ ሊፈፅሙ እንደሚችሉ ባህሪያቸው የአደባባይ ሚስጢር እየሆነ መጥቷል። በሀገራችን እየተካሄደ ያለው አስገራሚ ድርጊትም ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

አዎ!! “ቀበሮ የበግ ለምድ ለብሶ ፍየሌን ቀማኝ” እንዳሉ ሁሉ ህወሓት/ኢህአዴግ የነፃነት ካባ ለብሶ ታግሎ መንበረ ስልጣኑን ካመቻቸ በኋላ መልሶ የኢትዮጵያን ህዝብ ነፃነት የነጠቀና የመቶ ሽዎችን ሰማእታት አደራ የሰበረ የክህደት ስብስብ መሆኑን ከተግባሩ በላይ ሌላ ምስክር የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሁላችንም እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ የነፃነት ትግል ታሪክ ቢሆንም ታግሎ ያገኘውን የድል ችቦ በተደጋጋሚ በጥቂት ከሃዲዎች በአቋራጭ እየተነጠቀ፣ የተከፈለውን የነፃነት ዋጋ መስዋእትነት ውጤቱ ታጥቦ ጭቃ እየሆነ በመምጣቱ እነሆ ዛሬም ኢትዮጵያ እናታችን በዓለም ማሕበረሰብ ዘንድ የረሃብ፣ የጦርነት፣ የዝርፊያ፣ የአፈና፣ የጭቆናና የልመና ተምሳሌት ሆና እንድትታይ አድርጓታል።

ህወሓት/ኢሕአዴግ እንዳለፉት መንግስታት በህዝቡ ላይ የሚፈፅማቸው የጭቆና ተግባራት የሚያሳዩ ጭብጦች በጣም በርካታ ከመሆናቸው ባሻገር ሁሉም በዚህ ፅሑፍ ዘርዝሮ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረብ ለቀባሪ ማርዳት ስለሚሆንብኝ በቅርብ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት ሄጄ ሶስት ወር ያህል ቆይታዬ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውሬ በዓይኔ ያየሁዋቸውና ከህዝቡ አንደበት የሰማኋቸው አንዳንድ የብሶትና የቁጭት መገለጫዎች አጠናክሬ በተለይም ከምትወድዋት እናት ሀገራችሁ ርቃችሁ ባህር ማዶ በስደት ዓለም ለምትገኙ ውድ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼና እህቶቼ በዚያች ምድር ምን ዓይነት ዓይን ያወጣ ግፍ እየተፈፀመ እንደሆነና ህዝባችን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ “ማን ያርዳ የቀበረ ማን ይናገር የነበረ” ነውና ለግንዛቤ ያህል ይጠቅማሉ ብዬ ያመንኩዋቸው ሃሳቦች ለናንተም ለማካፈል በዋና ዋና ጉዳዮች ብቻ በማተኮር በዚሁ ክፍል አንድ ፅሑፌ በአጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

<u>ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ምን ዓይነት ስርዓት ነው?</u>

ኢ.ሕአዴግ ምን ዓይነት ስርዓት እንደሆነ ከምናይበት መንገድ ውስጥ በሚከተለው አላማውና በየጊዜው በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሕጎች፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴው፣ እንዲሁም ታሪካዊ አመጣጡና አበቃቀሉ የመሳሰሉ ከዋና ዋናዎቹ መስፈርቶች ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ሶስት ነጥቦች ሰፊ ትንተናና ሞያዊ ጥናት ስለሚያስፈልጋቸው አሁን ወደ ዝርዝር ትንተና ሳልገባ በአጭሩ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ። ሌላ ጊዜ በቀጣዩ ፅሑፌ ዘርዘር ባለ መልኩ ለማቅረብ ጥረት አደርጋለሁ።

ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ወይም የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት በባህሪው ሁለት ስለት ያለው፣ ቀለም እየቀያየረ፣ አዳዲስ የተስፋ ቃላትን እየፈበረከ፣ የፖለቲካ ስልጣን ሞኖፖል እየገነባ፣ የሀገሪትዋን አንጡራ ሀብት እንደ ምስጥ እየቦረቦረ፣ የህዝቡን ማሕበራዊና ህሊናዊ ፋብሪክ እያፈረሰና እየበወዘ የሁሉም ዜጋ የግልም ሆነ ቡድናዊ ነፃነቱን ነጥቆ በአንድ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከራጢት ውስጥ አስገብቶ ዘላለማዊ ስልጣኑን ለማረጋገጥ አልሞና ታጥቆ የተነሳ ስብስብ ነው። በየጊዜው የሚያወጣቸው ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ የመንግስት አወቃቀሩም ሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴው ሁሉም ከላይ ከተጠቀሰው ሰይጣናዊ አስተሳሰብ የሚመነጩ ናቸው።

<u>ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ሕብረተሰቡን ለመቆጣጠርና ብሎም የስልጣን ዕድሜውን በሞኖፖል ይዞ ለመቀጠል የሚወስዳቸው አፋኝ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?</u>

ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ የሕብረተሰቡን ስነ ልቦናና ህሊናዊ አመለካከት ለመቆጣጠር ሲል 85 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ደጋፊ/አባል፣ ማሐል ሰፋሪ፣ ጠላት/ተቃዋሚ ብሎ በሶስት ዘርፍ

ፈርጅታል። አባል ወይም ደጋፊ ማለት የሌላውን ዜጋ መብት ለማፈን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ተልእኮ ይዞ የሚንቀሳቀስ ታማኝ አገልጋይ ማለት ነው። ለምሳሌ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በግልፅ በተግባር እንደታየው አንድ የህወሓት/ኢ.ሕአዴግ አባል ወይም ደጋፊ በስሩ ከ5 — 10 ንፁሃን ዜጎች እንቅስቃሴያቸውን በነቂስ እየተከታተለ እንዲሰልል፣ እንዲያደረጅ፣ በመደለል ወይም በማስፈራራት ለገዢው ፓርቲ እንዲመርጡ ሲያደርግ ቆይቷል። እምቢ ካለ ደግሞ ለበላይ አካል ሪፓርት እያደረገ በቀጥታም ሆነ በስውር እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያድርግ ነው። አሁንም ይህ ዓይነቱ የስለላና የአፈና መረብ በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ ይገኛል።

ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ በኢትዮጵያ ምድር ያለ እርሱ ሌላ ትርጉም ያለው፣ ለህዝብ አማራጭ ሀይል ሊሆን የሚችል፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ስር የሰደደና ተቀባይነት ያገኘ፣ በሰላም የሚታገል ሀገር በቀል የፓለቲካ ድርጅት እንዲኖር ፈፅሞ አይፈልግም። ከዚህ በመነሳት ማሐል ሰፋሪ ወይም ተቃዋሚ ተብሎ የተፈረጀውን ወገን ሁሉ ቢችል የኢ.ሕአዴግ አባል እንዲሆን መጣር ካልሆነ ደግሞ በጠላትነት ፈርጆ ሰበብ አስባብ እየፈለጉ አንገት የሚያስደፋ እርምጃ መውሰድ ነው።

ሰሞኑን በሀገር ውስጥ ሰላማዊ የትግል መርሕ ተከትለው፣ ህዝብንና ሕግን አምነው፣ ሕጋዊ ፍቃድ ተሰጥቷቸው በሕግ የሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላት ላይ እየደረሰ ያለው የመንጥር ዘመቻ መነሻው ምን እንደሆነ ለሁሉም ወገን ግልፅ ይመስለኛል። ኢ.ህአዴግን የሚቃወም ፀረ ሰላም፤ ፀረ ህዝብ ባጠቃላይ ፀረ ኢትዮጵያ ነው በማለት ማንኛውም ዜጋ የመፃፍ፤ የመደራጀት፤ የመናገርና በማንኛውም መልኩ እንዳይንቀሳቀስ በቁጥጥር ተይዟል፡፡ ህዝቡ እርስ በርሱ እንዳይተማመንና ወደ ፍፁም ፍርሃትና ሽብር እንዲገባ ተድርገዋል፡፡ ዛሬ በመላው ሃገሪቱ ከየትኛውም ጊዜ በላይ በባሰ ሁኔታ የአፈና እና የስለላ የቁጥጥር መዋቅር ተዘርግተዋል፡፡

<u>እውነት ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ልማታዊ መንግስት ነው?</u>

ሌላው የህወሓት/ኢ.ህአዴግ ማደናገሪያ ዘዴ በልማት ስም ህዝቡን የህልም እንጀራ ማብላት ነው። በዚሁ የሶስት ወር ቆይታዬ ብዙ አስቂኝና አዛሳኝ ሁኔታዎችን ለማየት ችያለሁ። በጣም አስቂኝ ነገር ሆኖ የታየኝ አቶ መለስ ዜናዊ በተለመደው አንደበታቸው የህዝቡን ቀልብ ሊስብ ወይም ሊያሳስት ይችላል ብለው የሚገምቱትን በየጊዜው አሽብራቂ ቃላትን እየፈበረኩ እርስ በርሱ የሚቃረንና ከሀገሪትዋ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፈፅሞ ሊገናኝ የማይችል ነገር ለማመሳሰል አስቂኝ ድራማ ሲሰሩ ማየቴ ነው። በሞኖፓል የተቆጣጠሩትን የብዙሃን መገናኛዎች ነጋ ጠባ የሚያወሩት ስለ ፈጣን የልማት ዕድገት፣ ተሃድሶ፤ የሚሊዮኔም ህዳሴ፤ ታላቁ የህዳሴ ግድብ፣ ትንሰኤ፤ ልማታዊ መንግስት፤ ልማታዊ ወጣት፤ ልማታዊ መከላከያ፤ ልማታዊ አርቲስት፣ ወዘተ ወዘተ የሚሉትን የድለላ ቃላት ህዝቡን አሰልችቷል፡፡

አቶ መለስ ስልጣኔን ሊያራዝምልኝ ይችላል ብለው የሚያስቡትን ነገር ተውኔት ከመስራት ወደኋላ እንደማይሉ ተደጋግሞ ተነግሮላቸዋል። አስታውሳለሁ ከ20 ዓመት በፊት ይመስለኛል ወደ አሜሪካን ሀገር ለጉብኝት መጥተው በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያንን ሰብስበው ውይይት በሚያካሂዱበት ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት የልማት ራዕይና ዕድገት ተጠይቀው ሲመልሱ "የኢትዮጵያ ህዝብ ከአስር ዓመት በኋላ በቀን ሶስት ጊዜ ይበላል። ከሃያ ዓመት በኋላ ደግሞ አማርጦ ይበላል" ብለው እንደነበር ይታወሳል። ዛሬም የሚሉን ይኸው ነው። "ድርብ አሃዝ የልማት ዕድገት አስመዝግበናል፣

ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ መካከለኛ ገቢ ካላቸው እንደነ ብራዚልና ኢንዶነዥያ የመሳሰሉ ሀገሮች ተርታ ትሰለፋለች፣ ረሃብ በቅርብ ጊዜ ታሪክ ሆኖ ይቀራል፣ ወዘተ "የመሳሰሉትን ምርጥ ምርጥ መዝገበ ቃላት እየመረጡ ያላንዳች ይሉኝታ በአደባባይ በመናገር ዓይናችሁን ጨፍኑና እናሞኛችሁ እያሉን ነው።

ልብ በሉ ወገኖቼ!! ዛሬ ህዝቡ የልማት ተጠቃሚ መሆንና በቀን ሶስት ጊዜ ወይም አማርጦ መብላትስ ቀርቶ ከጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ከግማሽ በላይ በቀን አንድ ጊዜ በልቶ ማደር አቅቶታል። በአንድ በኩል የንሮ ውድነት ጣሪያ ነክቶ ህዝቡ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል። የስራ አጥነት ቁጥር ብዛት፣ የስደተኛና የተመፅዋች ቁጥር፣ የዋጋ ንረት፣ የገንዘቡን ግሽበትና የብር የመግዛትና የምንዛሪ አቅም መውደቅ ተደማምሮ የኢኮኖሚውንና የንሮውን ቀውስ አባብሶታል። በሌላ በኩል ደግሞ ዓይን ያወጣ ሙሱና እና የተደራጀ የሀገሪትዋ ሃብት ዝርፊያ ለጉድ ነው። በአሁኑ ጊዜ ተሹሞ ያልበላ ሰው እንደ ሞኝ የሚቆጠርበት ጊዜ ላይ ነን ያለነው። ፍትሕ አልባ ስርዓት በነገሰበት ዘመን "ከሳሽ ከመሆን ይልቅ ተከሳሽ መሆን ይሻላል" የሚባልበት ዘመን ላይ ነው ያለነው።

በሀገር ቤት ቆይታዬ ከዚህ የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር ተያይዞ ስለ አንድ አስገራሚ ገጠመኝ ልንገራችሁና ወደ ሌላ ነጥቤ ልሻገር። በምእራብ ትግራይ ሽራሮ አከባቢ በኤክስቴንሽን ታቅፈው ከሚያርሱ ገበሬዎች አንዱ የሆኑት ነዋሪ የእርሻቸው ምርት አፍሰው ቤታቸው ይገባሉ፡፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ያካባቢው የመንግስት ባለስልጣናት ይመጡና "በተደረገልኝ እገዛ ምክንያት 90 ኩንታል አግኝቻለሁ ብለህ በቴሌቪዥን ተናገር" ይሏቸዋል፡፡ ሰውየው በባለስልጣናቱ ንግግር ተገርመው "እኔ ያገኘሁት 10 ኩንታል ነው። ያላገኘሁትን በውሸት ብናገር ጎረቤቶቼስ ምን ይሉኛል? ዋናው ነገር ደግሞ 80 ኩንታሉ የት አስቀመጥከው ብላ ባለቤቴ ብትጠይቀኝስ ምን ልላት ነው? እናንተ 80ውን ኩነታል እህል ከሰጣችሁኝ ምንም ችግር የለውም መናገር እችላለሁ። ነገር ግን ያልበላሁትን በልቼለሁ ብዬ መናገር ነገ ሟች ህሊናዬን ይወቅሰኛል" ነበር ያሉዋቸው ገበሬው፡፡ ታድያስ ወገኖቼ!! ድርቅንና ረሃብን እንደ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ አድርጎ በመጠቀም በዜጎች ህይወት ላይ የፖለቲካ ቁማር የሚጫወት መንግስት ውሸት ተናገሩ እያለ ቢያስፈራራ የሚደንቅ ይመስላችኋልን?

ሌላው የትዕዝብት ገፅታ ያየሁት በሽሬ እንዳስላሴ ግንቦት 5/2011 እ.ኤ.አ በ03 ቀበሌ አፍሪካ ሆቴል ፊት ለፊት በረካታ ወጣቶች የተሰበሰቡበት ነበር። እኔም ሁኔታውን ለመረዳት ጠጋ ብዬ ስመለከት በከተማው ቀደም ብሎ በቻይና ስለተሰራው አስፋልት ጥቂት ቀናት ሳይቆይ በመፈራረሱ የከተማውን ነዋሪ ህዝብ ቁጣ ቀስቅሶ አስፋልቱን እንደገና ሊጠግኑ ከመጡት ቻይናውያን ጋር ግብግብ ገጥሟል። "እናንተ አስፋልቱን አትጠግኑም ከከተማው ውጡልን፣ ከዚህ ልቀቅሉን" እያለ በምሬት ሲጮኽ ነበር የደረስኩት። የሰልፉ አላማ በአንድ በኩል አስፋልቱ በሚገባ አልተሰራም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የህዝብና የመንግስት በጀት በማይረባ አስፋልት ስም ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር ተዘርፈዋል የሚል ነው።

ይህንን መነሻ በማድረግ ህዝቡ ቻይናዎቹን ከአስፋልቱ መንገድ ካስለቀቀ በኋላ ቅሬታውን በሰላማዊ ሰልፍ ለመግለፅ እንዲችል ፍቃድ ለመጠየቅ ወደያውኑ 15 አባላት ያለው ጊዚያዊ ኮሚቴ መርጦ ወደ አስተዳደሩ ላከ። ይሁን እንጂ የተላኩት ሰዎች ጉዳያቸውን በአግባቡ ቢያስረዱም ከአስተዳደሩ የተሰጣቸው ምላሽ ግን እንደጠበቁት አልነበረም። "ይህ ዓይነት ሃሳብ የፀረ ትግራይ ሃይሎች ተላላኪዎች ሴራ ስለሆነ በምንም ዓይነት መልኩ ሰላማዊ

ሰልፍ አይፈቀድላቸሁም፡፡ ደማችን ከፍለን ያመጣነውን ዴሞክራሲ በዋዛ ፈዛዛ ወይም በሰላማዊ ሰልፍ ሊነጥቁን አንፈቅድም" የሚል ቁጣና ዛቻ የተሞላበት መልስ ነበር።

ወከባውና አፈናው በዚህ ብቻ አላበቃም። ሰላማዊ ሰልፉን የጠነሰሱት የዓረና አባላት ናቸው በሚል ሰበብ በአከባቢ በተለያዩ የግል የስራ ዘርፍ ተሰማርተው በአረና መድረክ ውስጥ ተደራጅተው በሚንቀሳቀሱት ወጣቶች በየቀኑ የሚደርስባቸው ወደር የለሽ ግፍና በደል ከሚቋቋሙት በላይ መሆኑን ካራሳቸው አንደበት ለመረዳት ችያለሁ። በተለይ የደህንነት አባላቱ በየሄዱበትና በገቡበት ቦታ ደረስ እየሄዱ በማዋከብ የግል ስራቸውም ጭምር ሊሰሩና በአገራቸው በሰላም ሊኖሩ ያልቻሉበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ያላቸው ምርጫ እሺ ካሉ አረናን ትተው ህወሓት ውስጥ እንዲገቡ ካልሆነ ደግሞ የመጨረሻ ዕድላቸው ሀገር ለቀው እንዲሰደዱ ወይም እስር ቤት ገብተው ታጉረው መኖር ነው ዕጣ ፋንታቸው።

ከተለያዩ የስርዓቱ ሰለባ ከሆኑት ወገኖች እንደተረዳሁት አንድ ሰው በተለይም ወጣቱ ትውልድ የሌላ ድርጅት አባልና ደጋፊ ነው ተብሎ ከተጠረጠረ ወይም የህወሓትን አመለካከት ያልደገፈ ወይም አባል ያልሆነ ሁሉ እንደ ዜጋ በነፃ የመኖር ዋስትና የለውም። የዩኒቨርስቲ ደጃፍ አይረግጥም፣ ስራ የማግኘት ዕድሉ የተዘጋ ነው፣ ከውጭ የሚመጣው እርዳታና ጥቅማ ጥቅም አያገኝም፣ ሌላ ቀርቶ ንግድ ለመክፈት ወይም ቤት ተከራይቶ ለመኖር እንኳን ዕድሉ የጠበበ ነው። ከጥቅማ ጥቅም መገለል ብቻ አይደለም በተለያየ ተፅዕኖ ከሕብረተሰቡም ጭምር እንዲገለል ስለሚደረግ ሳይወድ በግድ የሞቀ ቤቱን ወይም የሚወዳት ሀገሩን ለቆ እንዲሰደድ ወይም ቦታ እንዲቀይር ግድ ይሆንበታል።

የተከበራችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ!! እኔ ድንገት በተዘዋወርኩባቸው ቦታዎች ያየሁትን አሳዛኝ ክስተቶች ለመጥቀስ ሞከርኩ እንጂ በአሁኑ ጊዜ በመላ ሀገሪቱ ሰበብ አሳስባብ እየተፈለገበት በእስር ቤት እየማቀቀ የሚገኘው ዜጋ ስፍር ቁጥር የለውም። በትግራይ በዓረና ስም፣ በኦሮምያ በኦነግ ስም፣ በኦጋዴን በኦብነግ ስም፣ በመድረክ ስም እንዲሁም የተለያየ ታርጋ እየተለጠፈባቸው ለአቶ መለስ ዜናዊ ስልጣን ያሰጋል ተብሎ የተጠረጠረው ሁሉ "ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" በማለት ገና ከእንጭጩ እንዲጠፉ ብሎም አንገቱ እንዲደፋ እየተደረገ ይገኛል። በተለይም በእውቀት ብስለትና የአላማ ፅናት ያላቸው ወጣት ሙሁራን አዲሱን ትውልድ ያንቀሳቅሳሉ ብለው ስለሚፈሩ በአጭሩ እንዲቀጩ ያደርጋሉ።

በፅሑፌ መግቢያ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ዛሬ በእስር ቤት ፍዳውን እያየ ያለው የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ብቻ አይደለም። በአንድ በኩል በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ በሌላ በኩል ደግሞ ብሶቱን እንዳይናገር፣ የችግሩ መፍትሄ አማራጭ መንገድ እንዳይፈልግ፣ እንዳይፅፍና በተወለደባት ምድር በነፃ እንዳይንቀሳቀስ ልሳኑ ተሸብቦ የቁም እስር የተፈረደበት 85 ሚሊዮን ህዝብም ጭምር ነው። አለ መታደል ሆነብን የደርግ የመንጥር ዘመቻ ዛሬ መልኩን ለውጦ መጥቷል። የደርግና የስታሊን አብዮታዊ የቀይ ሽብር እርምጃ ዛሬም መልኩንና ስልቱን ቀይሮ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስም በይፋ በአዋጅ ተደግፎ በመላ ህዝባችን ላይ የማሸበርና የማሸማቀቅ ተግባር እየተፈፀመብን ይገኛል። ኩሩና ለነፃነቱ እምቢ ባይ ህዝባችን ዛሬ በአፈ ሙዝ አገዛዝ ስር ወድቆ የጥቂት አምባ ገነን መሪዎች ብሎም የአንድ ቤተሰብ መጫወቻ ሆነዋል። የብዙ ሃይማኖትና ብሄር ብሄረሰብ የጋራ እናት የሆነችውን ሀገራችን ዛሬ ባለቤት አጥታ አንጡራ ሀብትዋ እየተቦረቦረ፣ ለም መሬትዋ እየተሸነሸነ፣ ሉዓላዊነትዋ እየተደፈረ በግልፅ የባዕዳን መጠቀሚያና የጥቂት ባለስልጣናት መበልፀጊያ ሆናለች።

ታዲያ ይህ ከሆነ ሐቁ!! አባቶቻችን መስዋእትነት ከፍለው አንድነትዋንና ሉዓላዊነትዋን ጠብቀው ያቆዩልንን ሀገር አሁን ማን ይሚኅትላት? ህዝባችን ነፃነቱንና ክብሩን ተነጥቆ በሽብር አዋጅ ሲታመስና የጥቂት ጨካኝ መሪዎች መጫወቻ ሲሆን ማን ከጎኑ ቆሞ አቤት ይበልለት? ዜጎቻችን የሕግ የበላይነት ይከበር፣ ለሁላችን በጋር የሚያስተናግድ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ይፈጠር፣ አፈናና አድልዎ ይቁም!! ስላሉ ብቻ እንደ ዉሻ ከያሉበት እየታደኑ እስር ቤት ሲወረወሩ ማን ጥብቅና ይቁምላቸው? ወይስ እንዲሁ በማይረባ ምክንያት ተለያይተን በየተራ እየተቀጠቀጥን እንኑር እንዴ? ለመሆኑ ይቺ ሀገር አንድ ጋዳፊ ዓይነት መሪ ብቻ ነው እንዴ የወለደችው? ሌላ የበለጠ ጥበብ፣ ጀግንነትና ፅናት ያለው ዜጋ የለም ማለት ነውን? እናስብበት?

በዚህና በሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮች ዙርያ በሁለተኛው ክፍል ፅሑፌ እስከምንገናኝ ድረስ ለዛሬ መልካም አዲስ አመት መልካም የመስቀል ደመራ ይሁንላችሁ እላለሁ፡፡

በዚሁ አጋጣሚ ሰሞኑን በትግራይ ክልል በመኪና አደጋ ሂወታቸው ላጡና ከፍተኛ የአካል ጉዳት ለድረሰባቸው ታጋዮችና የትግራይ ፖሊስ ኦርኬስትራ አባላት ወገኖቻችን ሁላችን እንድናስባቸው ይገባል ብየ አምናለሁ፡፡ ጉዳያቸውም ባአግባቡ እንዲጣራ ግፊት መደረግ አለበት እያልኩኝ ለቤተሰቦቻችውና ጓደኞቻቸው ብርታትና ፅናትን እመኛለሁ፡፡

ኢ-ሜይል sgbtsait@gmail.com

ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኑር !!!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!